# የዶ/ር ዓቢይ ተግዳሮቶች
## ባይሳ ዋቅ ወያ

የጠቅላይ ሚኒስትራችን ዶ/ር ዓቢይን መሾም ተከትሎ በመከሰት ላይ ያለው የለውጥ ሂደት በተለያዩ የማህበረሰባችን አባላት የተለያየ ትርጉም እየተሰጠው ይገኛል። አንዳንዶቹ፣ ሰውዬው ኢሕአዴግ ኮትኩቶ ያሳደጋቸው በመሆኑ የድርጅቱን ፖሊሲ ሊቀይሩ አይችሉም ሲሉ ሌሎች ደግሞ፣ ምንም እንኳ ከሥርዓቱ የበቀሉ ቢሆንም፣ ከዚህ በፊት በሌሎች አገራት በታሪክ እንደታየው ሁሉ ኮትኩቶ ያሳደጋቸውን ሥርዓት ለመቀየር ይችላሉ ይላሉ። ሁላችንም በተለያየ ጭንቅላት ስለምናስብ፣ የተለያየ ግምት መውሰዳችን አያስገርምም። በበኩሌ፣ ጠ/ሚኒስትሩ ለውጥ ለማምጣት ፍላጎቱም ቅንነቱም አላቸው ባይ ነኝ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከተሾሙ በኋላ ይዘው ከተነሷቸው መሪ አባባሎች መካከል ደጋግመው የሚያሰሟቸው **"መደመርና" "ይቅርታ"** የተባሉ ቃላት የብዙዎቻችንን ቀልብ ስበዋል። ብዙዎቻችንም እንደመሰለን በተለያየ መንገድ ተርጉመናቸዋል። የተለያየ ትርጉም መስጠታችን በራሱ ምንም ክፋት ባይኖረውም፣ እንደተረዳነው በተግባር ሳይተረጎሙ ከቀሩ ግን ቅሬታን ማስከተላቸው አይቀሬ ነውና የነዚህን መሪህ ትክክለኛ ይዘት ከወዲሁ ማወቁ አስፈላጊ ይመስለኛል። ትክክለኛ ትርጉሙን የመሪሁ የፓቴንት ባላቤት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዝርዝር ያስረዱናል ብዬ እገምታለሁ። እስከዚያው ድረስ ግን እኔን እንዴት እንደገባኝ ለማስረዳት እሞክራለሁ።

ለኔ እንደሚገባኝ **"መደመር"** ማለት <u>አንድ ላይ መሆን እንጂ ተጨፍልቆ አንድ ወጥ መሆን ማለት አይደለም።</u> እኔ መደመርን በትዳር አስመስላለሁ፣ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ከተፋቀሩ በኋላ ትዳር መስርተው አብሮ በደስታ መኖር ማለት ነው። ትዳር ከመሰረቱ በኋላ ወንዱም የተባዕታይ ጾታውን፣ ሴቷም የአንስታይ ጾታዋን እንደያዘች አብረው ይኖራሉ እንጂ ሁለቱ ተደምረው አንድ ግዑዝ ጾታ አይወጣቸውም። **የመደመርን** አተገባበር በኢትዮጵያ የፖሊቲካ ሁኔታ ውስጥ የተመለከትን እንደሆነ፣ ያገሪቷ ሰማኒያ አምስት ብሄሮች በእኩልነትና በፍቅር ላይ በተመሰረተ አንድነት አብረው ይኖራሉ ማለት ነው እንጂ እርስ በርሳቸው ውስጥ ተቀላልጠውና ተጨፍልቀው አንድ ወጥ የሆነ ብሄር ይሆናሉ ማለት አይደለም። ብዙዎቻችን ግን "መደመር"ን **"አንድ መሆን"** ከሚለው ጋር እያጋጬን የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ እንደ "አንድ ወጥ ብሄር" አብሮ መኖር የሚጀምር ይመስለናል። በጣም ጥሩ ምኞት ነው። "ሳያድለን" ቀርቶ ግን ሰማንያ አምስት ሆንን እንጂ እንደ ሱማሌዎች አንድ ብሄር፣ አንድ ቋንቋ፣ አንድ ኃይማኖትና አንድ ባንዲራ ብቻ ቢኖረን እሰየው ነበር። ግን አልሆነም። ስላልሆነ ደግሞ ማዘን የለብንም። በአግባቡ ከተጠቀምንበት፣ የተለያዩ ብሄሮች ባንድ አገር ውስጥ መኖር ተዝቆ የማያልቅ ሃብትና ተደንቆ የማይጠገብ ውበት ነው። አገር ደግሞ የተለያዩ ብሄሮችን ስላቀፈች ብቻ ለግጭት ብሎም ለመከፋፈል አትዳረግም፣ አንድ ወጥ ሕዝብ፣ አንድ ቋንቋና አንድ ኃይማኖት ስላላትም ደግሞ ከግጭትና ብሎም ከመገነጣጠል አትድንም።

**"ይቅርታ"** የሚለው የዶ/ር ዓቢይ መሪህም እንደዚሁ በተለያየ መንገድ እየተተረጎመ ይገኛል። አብዛኛው ሕዝብ "ይቅርታን" "ግራ ጉንጭህን በጥፊ ለመታህ ቀኙን አዙርለት" ከሚለው ኃይማኖታዊ መሪህ ጋር ያያይዙታል። ባገራችን ውስጥ በተለይም ላለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት፣ የሥልጣን ወይም የሙያ ወንበራቸውን ያላግባብ በመጠቀም ሰፊውን ሕዝብ ሲያስሩ፣ ሲገርፉ፣ ሲያሰቃዩና ሲገድሉ የነበሩትን ወንጀለኞች "ያለፈው አልፏል፣ የሞቱትን ለመለስ አይቻልም፣ ሕይወት ግን መቀጠል ስላለበት ይቅር ተባብለን ያለፈውን ፋይል በሙሉ ዘግተን አዲስ ምዕራፍ እንክፈት" ማለት ነው ብለው የደመደሙም አይጠፉም። እንደሚገባኝና ከጠቅላይ ሚኒስትሩም ንግግር እንደገመገምኩት ከሆነ ግን፣ እሳቸው እየደጋገሙ **"ሕገ መንግሥቱ በሚፈቅደው መሠረት"** ስለሚሉና፣ ሕገ መንግሥቱ ደግሞ፣ ወንጀል የሰራ ማንኛውም ዜጋ በሕጉ (ወንጀለኛ መቅጫ) መሰረት ይቀጣል ስለሚል፣ ወንጀል የፈጸሙ ግለሰቦች ለፍርድ ቀርበው ተገቢውን ቅጣት ይቀበላሉ ማለት ነው። በምድራዊው ፍርድ ቤት ተፈርዶባቸው ቅጣታቸውን እየፈጸሙና በመታረም ላይ እያሉ ግን፣ የሚያሳዩት ጸጸትና የመታረም ፍላጎት ታይቶ <u>ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት</u> ርዕሰ ብሄሩ ምህረት ሊያደርግላቸው ይችላል ማለት ነው እንጂ እንደ ሰማያዊው ሕግ "ኃጢአታችሁ ሁሉ ተሰርዮላችኋል" ተብለው ከቅጣት ይድናሉ ማለት አይደለም።

ለመንደርደርያ ያህል እነዚህን ሁለት የጠቅላይ ሚኒስትሩን መሪህ ቃላት አወሳሁ እንጂ፣ በዚህ ጽሁፌ ላጋራችሁ የፈለግሁት ዓቢይ ነገር **ዶ/ር ዓቢይን ከሚያጋጥሙት ተግዳሮቶች ጥቂቶቹን** ለማንሳት ነው። ዶ/ር ዓቢይ የፖሊቲካ ሥልጣን ከጨበጡ ጥቂት ወራት ብቻ ቢሆንም፣ በዚች አጭር ጊዜ ውስጥ የፈጸሟቸውን ተግባሮች እንደ አንድ ተቆርቋሪ ዜጋ ከዳር ሆኜ ስገመግመው በጣም አመርቂ ነው ባይ ነኝ። ዶ/ር ዓቢይና የዓላማ ግብረ አበሮቻቸው ማለትም በተለምዶ "የለማ ቡድን" በማለት የሚታወቁት፣ በኢሕአዴግ ውስጥ ምን ዓይነት የፖሊቲካ ጁዶ ሠርተው በአሸናፊነት እንደወጡ ባናውቅም፣ ዛሬ በተግባር እንደምናየው ከሆነ ግን፣ በርግጥም ጉልህ የሆነ የፖሊቲካ አቅጣጫ ለውጥ እየቀየሱ ነው። በህወሓት የበላይነት ዘመን የታሰሩትንና ሞት እንኳ የተፈረደባቸው የፖሊቲካ እስረኞች ሳይቀር ተፈትተዋል፣ የዜጎችን ሕገ መንግሥታዊና መሰረታዊ ሰብዓዊ መብቶችን የጣሱት ዓዋጆች ተነስተዋል። በሚቀጥለው መደበኛ ምርጫም ተፎካካሪ ኃይላት ያላንዳች መሰናክል እንዲሳተፉበት ቃል ተገብቷል። በጥቂት ወራት ውስጥ ባልታሰበ አኳኋንና ፍጥነት እየተጓዝን ስለሆነ ቆም ብለን ለማጣጣም እንኳ ጊዜ አጥሮናል። ግን ደግሞ እውን ነው። ደስ የሚል ዕውኔታ!

በተለምዶ “የለማ ቡድን” እየተባለ የሚጠራው ከአንጋፋዎቹ የድርጅቱ አባላት በዕድሜ ብቻ ሳይሆን ባስተሳሰብም ለየት ያሉት እነዚህ ለሕዝብ ተቆርቋሪ የሆኑ ቡድኖች ለዛሬ ይህ ነው የማይባል የሕዝብ ድጋፍ እንዳላቸው የሚይሳይ ባለፈው ሳምንት በመስቀል አደባባይ በፈቃደኝነት ወጥቶ የድጋፍ ድምጹን ሲያሰማ የነበረው በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ ሕያው ምሥክር ነው። በዚያው አንጻር ደግሞ ጥቂት በቡድኑ ድል ጥቅማቸው የተነካባቸው ግለሰቦች/ቡድኖች ያንን የደስታ ድባብ የጅ ቦምቦችን በመወርወር ለማበላሸት ሲሞክሩም አይተናል። ማንኛውም የፖሊቲካ ሥርዓትና አስተዳደር መላውን ሕዝብ ሊያስደስት ስለማይችል፣ ለውጡን የማይደግፉ ወገኖች መኖራቸው ተፈጥሮአዊ ነው። የተቃውሞ ድምጽን ግን <u>በሰላማዊው መንገድ ማሰማት ሲቻል</u> “ቦምብ” ብወረውር የበለጠ ተሰሚነት ይኖረኛል ብሎ ማሰብ ግን ጊዜው ያለፈበት የትግል ዘዴ ብቻ ሳይሆን፣ በዛሬው ዓለም አቀፋዊ ቋንቋም “ሽብርተኝነት” ነው። ይህ ደግሞ በብሔራዊ ሕጎች ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ሕግም ከባድ ቅጣት የሚያስከትል ወንጀል ነው። እነዚህን ዓይነት ምናልባትም ጥቅማቸው ከተነካባቸው ወገኖች የሚሰነዘሩትን ጥቃቶች ራስን ማዳን የዶ/ር ዓቢይ መንግሥት ዋነኛ ተግዳሮት ይመስለኛል።

ከዚሁ ባልተናነሰ መልኩ የዶ/ር ዓቢይን መንግሥት የሚገዳደሩ በቅርጽና ይዘታቸው ብቻ ሳይሆን በአፈጻፀም እንዲሁም በጊዜ ገደብ ሊፈረጁ የሚችሉ ብዙ ክስተቶች አሉ። ከነዚህ ተግዳሮቶች ጥቂቶቹን በጊዜ ገደብ መነጽር ለማየት ብንሞክር፣ <u>**ባጭር ጊዜና**</u> <u>**በረጅም ጊዜ**</u> ሊፈጸሙ የሚችሉ ብለን ልንከፍላቸው እንችላለን።

**ባጭር ጊዜ** መፍትሔ ሊገኝላቸው፣ ግን ደግሞ እጅግ በጣም አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች አንዱ የዜጎችን ሕገ መንግሥታዊና መሰረታዊ ሰብዓዊ መብቶችን ማክበር ነው። ይህ የመንግሥት ተቀዳሚ ግዴታ የሆነና መንግሥት ባጭር ጊዜ ውስጥና በዝቅተኛ ወጪ ሊያረጋግጥ የሚችል ተልዕኮው ነው። ከመንግሥት በኩል የሚያስፈልገው ዜጎች በሕገ መንግሥቱ ውስጥ የተደነገጉትን መብቶች ሳይሸራረፉ እንዲጠቀሙበት ማድረግ ብቻ ነው። ለዚህ ሁሉ ዋናው ተፈላጊ ነገር <u>የመንግሥት ቅንነትና ፍላጎት</u> ብቻ ነው። ዕቅዱን በሥራ ለማዋል፣ ጎጂ ዓዋጆችን መሠረዝና አዳዲስ የሕዝቡን መብት እንዲከበሩ የሚረዱ ሕጎችን ማውጣት ብቻ በቂ ነው። በተጨማሪም መንግሥት በሰው ልጆች መብቶች ተሟጋቾችና የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ (ለምሳሌ የተባበሩት መንግሥታት የሰው ልጆች መብት ኮሚሽኔር) እየተደገፈ ባገሪቷ ያሉትን የሕግና የፍትሕ ተቋማት እንዲሁም በፖሊስ ማሠልጠኛዎችን በመደበኛ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ትምህርት እንዲሰጡ ማድረግ ነው። ይህ ከኤኮኖሚ አንጻር ሲታይ በጣም ዝቅተኛ ወጪ የሚጠይቅ፣ ግን ደግሞ ላገሪቷ ዕድገት ጽኑ መሰረት የሚሆን ድርጊት ነው። **የሕዝቡ ድርሻ መብቱን አውቆ መንከባከብና በመንግሥት እንዳይጣሱበት መከላከል ብቻ ነው።**

በኤኮኖሚው መስክ አጥጋቢ ለውጥ ለማምጣት ግን **ረጅም ጊዜና ከፍተኛ ወጪ** ያስፈልጋል። ያገራችን ሕዝብ ግን ዛሬም እየተራበ ስለሆነ፣ “ከተወሰኑ ዓመታት በኋላ ኤኮኖሚያችን ሲያድግ በደንብ በልተህ ታድራለህ” ብሎ ለማባበል አስቸጋሪ የሚሆን ይመስለኛል። ዛሬ በመስቀል አደባባይ በነቂስ ወጥቶ ድጋፉን የሚያሳየው ሕዝብ ማታ ወደ ጎጆው ሲመለስ ገበታ ላይ ዳቦ ካላገኘ፣ በሚቀጥለው ጊዜ ወደ መስቀል አደባባይ ለመምጣት ፍላጎቱ እንኳ ቢኖረው ጉልበት ሊያጥረው ይችላል። ተቃዋሚ ኃይሎችም እንዲህ ዓይነቱን “ክፍተት” ጎልተው እያሳዩ ስለሚቀሰቅሱ፣ የተራበውም ሕዝብ ቀስ ብሎ ከደጋፊነት ወደ ተቃዋሚነት ሊሸጋገር የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። ይህ ተፈጥሮያዊ የሆነ የሰው ልጆች ባሕርይ ነው። ተፈጥሮያዊ የማይሆነው ግን፣ ችግሩ እየታወቀ፣ መንግሥት አስፈላጊውን መፍትሔ በጊዜ ለማቅረብ ሳይችል ሲቀር ነው።

የሕዝቡን የኑሮ ደረጃን ከፍ ለማድረግና ባጠቃላይ ያገሪቷን ኤኮኖሚያዊ ሁኔታ ለማሻሻል **መንግሥትም ሕዝብም እኩል ኃላፊነት አላቸው።** መንግሥት ዜጎች ሠርተው በሰላም የሚኖሩበትን የተረጋጋ ሁኔታ ከመፍጠር ባሻገር፣ ሕዝቡን መሠረት ያደረገና ያማከለ የአገሪቷን የኤኮኖሚ ዕቅድ በተግባር ማቅረብና ሕዝቡም ያላንዳች መሰናክል በዕቅዱ ተጠቅሞ ራሱን የሚያሻሽልበትን ድጎማ ማድረግ አለበት። በሌላ አነጋገር፣ የዶ/ር ዓቢይና ቡድኑ ሥራ ላለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ፍልስፍና ስም ስንሄድበት የነበረው ጎዳና ወደታሰበው ግብ ስላላደረሰን፣ አዲስና የሕዝቡን ተሳተፎ ያረጋገጠ የኤኮኖሚ ፖሊሲ መቀየስ አለበት ማለት ሲሆን፣ ሕዝቡ ደግሞ ይህ አዲሱ ፖሊሲ የፈለገውን ያህል ህዝባዊ ቢሆንና የሕዝቡን ድጋፍ ቢያገኝም፣ ባጭር ጊዜ ውስጥ የኢትዮጵያን ሕዝቦች የኑሮ ደረጃ ተሻሽሎ ማየት እንደማይችል ከወዲሁ አውቆ ወገቡን ጠበቅ በማድረግ ለረጅሙ ፈታኝ ጉዞ መሰናዳት እንዳለበት ማስረዳት የሁላችንም የሥራ ድርሻ ይመስለኛል።

ባገራችን ለዘመናት የሰፈነውን ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ቀውስ ባጭር ጊዜ ውስጥ ሊሻሻል የማይችልና በጣም ረጅም ጊዜ የሚጠይቅ ነው። በተለይም የሚያመረቃ የከርሰ ምድር ሃብትና ምርቶቿንም በቀላሉ ለዓለም ገበያ የምታቀርብበት የባህር በር የሌላት አገራችን፣ አሁን ካለችበት የድህነት ማጥ ውስጥ ለመውጣት ቢያንስ ቢያንስ የአንድ ትውልድ ዕድሜ ይጠይቃል ብል ማጋነን አይሆንም። ታዲያ፣ እንዴት አድርጎ ነው መንግሥት የሕዝባችንን ፋታ የማይሰጠውን የረኃብ ጉዳይና ረጅም ዓመት የሚጠይቀውን የዕድገት ጉዞ አገጣጥሞ ሕዝቡን ማረጋጋት የሚችለው? ለኔ ይህ ዋነኛው ተግዳሮት ይመስለኛል። ችግሩን ደግሞ የሚያባብሱ እንጂ መፍትሄ የሚያቀርቡ ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች በጣም ጥቂቶች ናቸው። ላለፉት ሁለት ምዕተ ዓመታት የለመድነውም፣ በትንሹም ቢሆን የተገነባውን እያፈረስን ከዜሮ የመጀመር “አብዮታዊ” ባሕል ስለሆነ፣ በተገነባው ላይ ቀስ በቀስ ጡቦችን እየጨመርን ከፍ እያደረግን የመሄድ ባሕል ስለሌለን ተግዳሮቱ እጥፍ ድርብ ነው።

ከላይ እንዳልኩት፣ ያንድን አገር ኤኮኖሚያዊ ዕድገት በተግባር ለመተርጎም ትውልድን ይጠይቃል። እንደ ማህበረሰባዊ ሕጉም ከሆነ፣ ያንድን አገር ኤኮኖሚያዊ ለውጥ ያመጣው ትውልድ የዕድገቱ ተጠቃሚ የመሆን ዕድሉ በጣም ጠባብ ነው። የከርሰ ምድር ኃብት ያላቸው አገራት አንጻራዊ በሆነ ፍጥነት ለውጡን ያመጣው ትውልድ ተጠቃሚ ሆኖ እንደሁ እንጂ፣ የአብዛኞቹ ያደጉት አገራት ታሪክ የሚያሳየን፣ የዕድገቱን መሠረት የጣለና የተሰዋለት ትውልድ የዘራውን ዘር ፍሬ ለመብላት አልበቃም። ስለዚህ ዛሬ የኤኮኖሚ ዕድገትን የሚያረጋግጥ ፖሊሲ ቢቀየስና ሁላችንም አምነንበት የየራሳችንን ሚና መጫወት ብንጀምር፣ የምንዘራውን ዘር ፍሬ የሚበሉት ልጆቻችን ይሆናሉ ማለት ነው። ይህንን ነው እንግዲህ ዛሬውኑ ዳቦ ለሚፈልገው ሕዝብ ማስረዳት የሚከብደው። ዛሬ ፀሃይ ሲያቃጥለን የምንጠለለበትን ትልቅ ዛፍ የተከሉት አባቶቻችን ዛፎቹ አድገው አንድ ቀን ለልጆቻቸውና ለልጅ ልጆቻቸው ጥላ ይሆናሉ ብለው ከማሰብ ነው እንጂ በሕይወት ዘመናቸው ተጠቃሚ እንደማይሆኑ ያውቁ ነበር። እኛም ዛሬ እየተራብን ጉልበታችንን አፍስሰን የምንገነባት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ለልጆቻን ትደርሳለች ከሚል አንጻር መሆን አለበት ማለቴ ነው። ይህንን ፍልስፍና በረኃብ ለሚንገላታው ሕዝብ ለማስረዳት ግን በጣም አስቸጋሪ ይመስለኛል። ለዚህም ነው ከዶ/ር ዓቢይ ተግዳሮቶች ሁሉ በጣም ከባዱ ይኸኛው ነው የምለው።

ይህንን ረጅም የዕድገት ጉዞ በመጠኑም ቢሆን ለማሳጠር የሚቻል ይመስለኛል። አንዳንድ አገራት መቶ ዓመት የፈጀባቸውን ጉዞ አንዳንዶች ደግሞ በሩብ ምዕተ ዓመት ብቻ አመርቂ የዕድገት ደረጃ ላይ የደረሱ አሉ። ለስኬቱ የረዱትን ነባራዊ ምክንያቶች ለኤኮኖሚ ባላሙያዎች ልተውና፣ እንድ አንድ ግለሰብ ግን በተለያዩ አገራት ካስተዋልኳቸው ብነሳ፣ ዋናውን ሚና የተጫወተው የመንግሥት ትክክለኛ ፖሊሲ መቀየስ ብቻ ሳይሆን፣ ሕዝቡም መንግሥቱንና የቀየሰውን ፖሊሲውን አምኖበት ስለተቀበለና ከመንግሥት ጎን ሆኖ በተግባር ለመተርጎም ስለወሰነ ነው። ባገራችን ታሪክ ግን እስከ ዛሬ ድረስ ሁለቱም የተገጣጠሙበት ሁኔታ አልነበረም። በመጀመርያ ደረጃ በታሪካችን ውስጥ አንድም ጊዜ በሕዝብ ፈቃድና በሰላማዊ መንገድ ሥልጣን ላይ የወጣ መሪ አልነበረንም። ይባስ ብሎም፣ አዲስ መሪ ሥልጣን ላይ በወጣ ቁጥር የድሮውን ሥርዓት በሙሉ ገርስሶ ከዜሮ ስለሚጀምርና፣ አዲስ የሚቀይሰው ፖሊሲ ደግሞ ተቀባይነት አግኝቶ ወይም ፍሬ አፍርቶ ሳይታይ ሌላ መሪ መጥቶ ሲተካው ብዙ ምዕተ ዓመታትን አሳልፈናል። ይህ እንግዲህ አሁን ያለውን ኢሕአዴግን ጨመሮ ለዘመናት ስናስተናግደው የነበረው “አብዮታዊ ለውጥ” ሲሆን፣ ዛሬ ግን የሥልጣን ወንበሩን የተረከበው ቡድን ከዚያው ከሥርዓቱ የተወለደ በመሆኑ በታሪካችን ውስጥ ለመጀመርያ ጊዜ፣ ካለው ሥርዓት ጠቃሚ ጠቃሚውን ወስዶ፣ በሱ ላይ የሚገነባ አዲስ አመራር ሲፈጠር ማየቱ፣ ለረጅሙ ጉዞያችን ተስፋን ያሰነቀ ክስተት ይመስለኛል።

መንግሥትና ማህበራዊ ድረ ገጾች እንደሚዘግቡት ከሆነ የዛሬው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰማኒያ በመቶው (80%) ዕድሜው ከአርባ ዓመት በታች ነው። ይህ ያልታደለ ትውልድ ነው እንግዲህ በአግባቡ ሊማር ባለመቻሉና ተምሮም ሥራ ባለማግኘቱ ምክንያት የተገኘውን ቀዳዳ ተጠቅሞ አብዛኛውን ጊዜ በሕገ ወጥ መንገድ ያገሪቷን ብቻ ሳይሆን የተጎራባች አገሮችንም ድንበር እየጣሰ በሰሃራ በረሃና በቀይ ባሕር ውስጥ ሰምጦ መቅረቱን የዓለም የዜና ማሰራጫዎች የሚያሰሙን። የዚህን ትውልድ ማለትም የህብረተሰቡን 80% አጣዳፊ የኑሮ ደረጃን አሻሽሎ ካገር እንዳይፈልሱ የሚረዳ መርሃ ግብር መቀየስ ለዶ/ር ዓቢይ ትልቅ ተግዳሮት መሆኑ ጥርጥር የለውም። በኔ ግምት፣ መንግሥት በጥብቅ ካሰበበት፣ ለሁላቸውም ባይሆን ለአብዛኞቹ የሚሆን መፍትሄ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ሊገኝ ይችላል ብዬ አስባለሁ። 80% የማህበረሰቡ አካል ወጣት ነው ማለት፣ ያን ያህል ጥቅም ላይ ያልዋለ “የሠራተኛ ጉልበት”፣ ግን ደግሞ ትክክለኛ ፖሊሲ ቢቀየስ በዓለም ገበያ ላይ ከማናቸውም ሸቀጥ እኩል ቀርቦ ሊሸጥ የሚችል **ውድ ሸቀጥ** አለ ማለት ነው። ይህንን ምርጥ ሸቀጥ ከገዢዎች ጋር ለማገናኘት ነው እንግዲህ መንግሥት ገዢዎችን ማፈላለግ ባስቸኳይ መጀመር አለበት የምለው። ካለኝ ልምድ ተነስቼ ለማለት የምችለው፣ ይህንን ውድ ሸቀጥ በዓለም ገበያ ላይ ለመሸጥ አንዳችም ችግር አያጋጥመንም ባይ ነኝ። ዋናው ነገር የመንግሥትን ቁርጠኝነት ከባላሙያዎች በጎ ፈቃድ ጋር ማቀናጀት መቻል ብቻ ነው። ዶ/ር ዓቢይ ቁርጠኝነቱ አላቸው፣ ፈቃደኛ ባለሙያዎችም ብዙ ናቸው።

ሌላው፣ ላገራችን ኤኮኖሚያዊ ዕድገት ዕውን መሆን መንግሥት ለሚያደርገው ጥረት ከፍተኛ አስተዋጽዎ በማድረግ የተግዳሮቶቹን መጠንና ጥንካሬ በመጠኑም ቢሆን ያዳክማል የምለው፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ባገራችን በመካሄድ ላይ ባለው ለውጥ ውስጥ ተገቢ ሚናቸውን እንዲጫወቱ መንግሥት ሁኔታዎችን የማመቻቸት ጉዳይ ነው። ወደ ድርጊት ስንተረጉመው፣ አሁን ያለው ትውልደ ኢትዮጵያውያንን ባገሪቷ የንግድ ተቋማት፣ ማለትም በባንኮችና በኢንሹራንሶች እንዲሁም በሌሎች ተመሳሳይ ዘርፎች ውስጥ አክሲዮን እንዳይገዙ የሚገድበውን ደንብ መሻርና በምትኩ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ባለ ሃብቶች፣ ምናልባትም ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚኖሩ ዜጎች በተለየ መልኩ (ማለትም ለምሳሌ በውጪ ምንዛሪ) እነዚህ ተቋማት የሚሸጧቸውን አክሲዮኖች እንዲገዙ መፍቀድ ያስፈልጋል። ሌላው ከዚሁ ጋር ተጓዳኝ የሆነና መንግሥት አስፈላጊውን እርምጃ ከወሰደ ለተወጠነው ረጅም የዕድገት ጉዞ ተጨማሪ ስንቅ ይሆናል ብዬ የማስበው፣ የጣምራ ዜግነትን የመፍቀድ ጉዳይ ነው። ጣምራ ዜግነትን የሚከለክለው ያገራችን ሕግ ቢሰረዝ፣ ያለፈቃዳቸው ያገራቸውን መንግሥት ሕጋዊ ከለላ ባለማግኘታቸው ብቻ ምርጫ አጥተው የውጪ ዜግነትን የወሰዱትን ትውልደ ኢትዮጵያውያንን መልሶ ከትውልድ አገራቸው ጋር ያቆራኛል እንጂ አንዳችም አሉታዊ ጎን አይኖረውም። ለዚህም በያመቱ የውጪ ዜጋ ፓስፖርታቸውን ተጠቅመው ያለቻቸውን የዕረፍት ጊዜ በትውልድ አገራቸው ለማሳለፍ ወደ ኢትዮጵያ የሚጎርፉትን ትውልደ ኢትዮጵያውያንን ከማየት የበለጠ ምስክር ሊኖር አይችልም። በርካሽ ዋጋ ከሎስ አንጂሌስ ወደ ሓዋይ ሄዶ ደረጃቸው ከፍ ባሉ ሆቴሎች አርፎና

እጅግ በጣም ንጹህ በሆነ የውቅያኖስ ባሕር ዋኝቶ ከመመለስ ይልቅ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ሃያ ሰዓት ተጉዞ አገር ቤት ከዘመድ አዝማድ ጋር ሽሮውን በልቶ ቢመለስ የሚመርጥ ሕዝብን፣ አገሩን እንደከዳ ቆጥሮ የኢትዮጵያን ዜግነት መንፈግ ትርጉም አልባ ይሆንብኛል። ጣምራ ዜግነት ቢፈቀድ፣ ቁጥራቸው በጣም ብዙ የሆኑ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ውጭ አገር በነበሩበት ዘመን ያፈሩትን ሃብትና ያካበቱትን ልምድ ይዘው በመመለስ ለዕድገት ዘመቻው ተባባሪ ይሆናሉና መንግሥት ባስቸኳይ ያስብበት ባይ ነኝ።

ሌላው ተግዳሮት ደግሞ ዛሬ ከልምድ አልፎ ባሕል እየሆነ የመጣው የሙስና ጉዳይ ነው። ከዚህ የኅብረተሰብ ነቀርሳ የጸዳ ዜጋን ለማፍራት ቢያንስ ቢያንስ ያንድ ትውልድ ዕድሜ ያስፈልጋልና፣ ከላይ የተበላሹትን ብቻ መቅጠፍ ሳይሆን፣ ገና ከአፀደ ሕጻናት ጀምሮ ዜጎች አገራቸውን በቅንነት እንዲያገለገሉ የሚያስተምር ብሔራዊ የግብረ ገብ ትምህርት መርሃ ግብር መንግሥት ያላንዳች መዘግየት የረጅም ጊዜ ዕቅድ አድርጎ ማውጣት አለበት።

ተግዳሮቶችን ካነሳሁ አየቀር አንድ ሁሌም የሚያሳስበኝና ብዙ ጊዜ ለመጻፍ እየሞከርኩ ያልተሳካልኝን አሁን በዚህ አጋጣሚ ላነሳ የምፈልገው፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተግዳሮት ነው ብዬ የማስበውን እኛን አንጋፋውን ትውልድ የሚመለከት ጉዳይ ላጋራችሁ እፈልጋለሁ። በኔ ግምት፣ የኛ ትውልድ ምንም እንኳን በትግል ዘመናችን ውስጥ መሬት ላራሹን የመሰለውን የምዕት ዓመቱን ታላቅ ድል የተጎናፀፍን ብንሆንም በዚያው ልክ ደግሞ፣ በተቃውሞ ኩሬ ተወልደን በተቃውሞ ባሕር ውስጥ ያደግን በመሆናችን ማንኛውንም የመንግሥት እርምጃ በ**“ሆኖም ግን”** ሐረግ የማጠናቀቅ እንጂ ሙሉ ድጋፍ የመስጠት ልምድ የሌለን የተቃውሞ ትውልድ ነን። ዋናው መለያችን የማያግባባንን አጉልተን የሚያግባባንን ማሳነስ የምንወድ፣ የ “ሸ” እና “ቸ” ፊደላት አጠቃቀምን እንኳ ያገር ጉዳይ አድርገን ለልዩነቶቻችን ማስፊያ የምንጠቀም “ባንድ አገር፣ አንድ ባንዲራ፣ አንድ ቋንቋ” መሪህ ማደጋችን ነው። በዘመናችን ሙሉ የምንቃወመው እንጂ የምንደግፈው አንድም መሪ ስላልነበረን፣ ባለፈው ሳምንት በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር አንድ ሙሉ ትውልድ በነቂስ ወጥቶ ለአቦ ለማ ቡድን ያለውን ፍቅርና ሙሉ ድጋፍ ሲገልጽ እንኳ ባይናችን በብረቱ እያየን ተዓምር እንጂ እውን የማይመስለን ትውልድ ነን። አዎ! የተቃውሞ ትውልድ!

በኔ ግምት የዛሬው 80% ሕዝባችን ከኛ ካንጋፋዎቹ ትውልድ ለየት ያለ፣ ከክልልና ካገራችን ድንበር ባሻገር ዓለምን ለማየት የሚችል አመለካከት ያለው ትልቅ ኃይል ነው ብል ማጋነን አይሆንብኝም። ለዚህም ይመስለኛል የትውልዱ ምርት የሆኑት ዶ/ር ዓቢይ ስለመደመር ሲያወሱ፣ በዘመነ “ግሎባላይዜሽን” በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን ህዝቦች ብቻ ሳይሆን ጎረቤት አገሮችም ካልተደመሩ በቀጠናው የሚያመረቃ ዕድገት ሊገኝ አይችልም በማለት በሚጎበኟቸው አገራት ሁሉ ያለመታከት የሚያሳስቡት። ይህ ትውልድ ዕድሜ ልኩን ያሳለፈው “በፌዴሬሽን አስተዳደር” እና “በክልሎች አወቃቀር”፣ በአንድ ባንዲራ ሥር ሳይሆን በዘጠኝ የክልሎችና አንድ የፌዴራል፣ ባጠቃላይም አሥር የኢትዮጵያን ባንዲራዎች ሲያውለበለብ ያደገ በመሆኑ፣ ዛሬ በየቦታው የሚውለበለቡት የባንዲራዎች ብዛት የኔን ትውልድ የሚያንገበግበውን ያህል የሚያንገበግባቸው አይመስለኝም። ለዚህም ነው ባለፈው በመስቀል አደባባይ በተደረገው የድጋፍ ሰልፍ ላይ የአጼውም፣ የኢህአዴግም፣ የክልሎች፣ የኦነግ እና ሌሎች የማላውቃቸውም ባንዲራዎች ሲውለበለቡ ቢታዩም፣ በባንዲራዎቹ ብዛት የተነሳ በአውለብላቢዎቹ መካከል አንዳችም ዓይነት ችግር ሲፈጠር ያልተስተዋለው። ባንዱ ጥግ ያለው ወጣት የኦሮሚያን ባንዲራ ይዞ በአጫሉ ሁንዴሳ ዘፈን ረገዳውን ሲለው፣ በሌላው ጫፍ ያለው ደግሞ በቅድመ ኢህአዴግ የነበረውን ባንዲራ ይዞ በቴዲ አፍሮ ዘፈን እስክስታውን ሲያቀልጠው፣ ሌላው ቡድን ደግሞ የዘመነ ኢህአዴግን ባንዲራ ይዞ “ያመናል በለው” እያለ ሲጨፍር በቅንነት ለተመለከተ ሰው የአገሪቷ ዥጉርጉርነት ምንኛ ውብ እንደሆነ ይረዳል። “ባንድ ባንዲራ” መሪህ ሥር ላደግን ለኔ ትውልድ ግን የባንዲራውን ብዛት ስንመለከት ባገሪቷ ሕዝቦች መሃል መከፋፈልን ብሎም አገሪቷን ወደ መበታተን የሚያመራ ስለሚመስለን፣ ወገኖቻችን ሲደሰቱ እያየን አብረን ለመደሰት እንኳ አልቻልንም። ባንዲራዎች መብዛታቸው ጥሩ ነው ማለቴ ሳይሆን፣ ያለ ሕዝቦች ፈቃድና ስምምነት በዝተው እንዲገኙ “ሕዝቡን እንወክላለን” በሚሉ የፖሊቲካ ድርጅቶችና መሪዎች ተወስኖብናልና፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ የሚስማማበትን አርማ የያዘ አንድ ብሔራዊ ባንዲራ እስኪፈጠር ድረስ ዛሬ ላይ ሆነን የባንዲራዎቹ መብዛት ለሕዝቦቿ አንድነት ያሰጋል ብለን መስጋቱን እናቁም ለማለት ያህል ነው። የባንዲራዎች መብዛት ሕዝብን የሚከፋፍል ቢሆን ኖሮ ስዊዘርላንድ አንድ ሳይሆን ሃያ ሰባት አገር ሆና ነበርና!

በትውልድ መካከል ያለውን የአስተሳሰብ ልዩነትን ካነሳን ዘንዳ፣ አንድ በዚህ ሰሞን የተከሰተና ለኔ ትውልድ፣ እንኳን ሊዋጥልን ይቅርና ለማኘክ ያቃተንን “አገራዊ ጉዳይ” ለመጥቀስ እወዳለሁ። ይኸውም፣ የዶ/ር ዓቢይ ቦሌ ድረስ ሄደው የኤርትራውን የውጪ ጉዳይ ሚኒስትርን በክብር መቀበል ነው። ለኔ ትውልድ ይህ የዶ/ር ዓቢይ ድርጊት አገሪቷን ያዋረደ ነው። በፕሮቶኮሉ መሠረት የሥልጣን አቻነት የሚባል መሪህ ስላለ ወደ ቦሌ መሄድ የነበረበት ዶ/ር ወርቅነህ እንጂ ዶ/ር ዓቢይ መሆን አልነበረበትምና! የሚገርመው ግን፣ ከኔ ካንጋፋው ትውልድ ውጪ ይህንን የዶ/ር ዓቢይን ድርጊት በአሉታ ጎኑ የተመለከተ አልነበረም። ዶ/ር ዓቢይም አላፈሩበትም። 80% የኢትዮጵያ ሕዝብም (የዶ/ሩ ትውልድ) አላጉረመረመም። ለኔ ትውልድ ነው እንጂ ያልተዋጠው፣ ለዶ/ር ዓቢይማ፣ ገና የአስራ አምስት ዓምት ልጅ እያሉ ባልታወቀ ምክንያት ካገር ጠፍተው የነበሩ የቅርብ ዘመዶቻቸውን ሄዶ እንደመቀበል አድርገው የቆጠሩ ይመስለኛል። ለማለት የፈለግሁት፣ ክስተቶችን በራሳችን ትውልድ መነጽር ብቻ ሳይሆን፣ በዶ/ር ዓቢይ ትውልድም መነጽር ለማየት መሞከር አለብን ማለቴ ነው። ዶ/ር ዓቢይ ወደ ቦሌ የሄዱት ፕሮቶኮሉ

ጠፍቷቸው ሳይሆን፣ የኤርትራ ልዑካንን ከውጭ አገር እንደሚመለሱ ቤተዘመድ አድርገው ስለቆጠሩ ብቻ ይመስለኛል። ይህ ደግሞ የሞራል የበላይነትን እንጂ ድክመትን አያመለክትም። ፖምፔዎን ወይም ላቭሮቭን ሄደው ቢቀበሉ ግን ከፕሮቶኮል ሥርዓት ውጪ ከመሆን ባሻገር ራስንና አገርንም ማቅለል ይሆናል።

በትውልድ መካከል ሁሌም የተለያየ አመለካከት መኖሩ ተፈጥሮአዊ ነው። በኦሮሚኛ "humni ganama dhumaa, qalbiin galgala dhufaa, eesa abaakootii fuudheen waliiti qabee illalla" (ጉልበት ጧት ይመጣል፣ አስተውሎት ደግሞ ከመሸ ይደርሳል፣ እንዴት አባቴ አድርጌ ላገናኛቸው?" የሚል ተረት አለ። አንጋፋው ትውልድ አስተውሎቱ አለው፣ ጉልበት ግን ከድቶታል። ወጣቱ ትውልድ ደግሞ ጉልበቱ አለው፣ አስተውሎት ወይም ልምድ ግን አላዳበረም ለማለት ነው። ላንድ ማህበረሰብ ዕድገት ደግሞ <u>አስተውሎቱም ጉልበቱም እኩል አስፈላጊ ነው።</u> በመካከላቸው ምንም ዓይነት ክፍተት መፈጠር የለበትም። ጥበቡ ያለው ሁለቱን ማቀናጀት መቻል ላይ ነው። አንጋፋው ትውልድ ከወጣቱ ትውልድ የበለጠ የሕይወት ልምድ ስላለው ብቻ ራሱን ከፍ አድርጎና ሁሉን አዋቂ አድርጎ በማቅረብ የወጣቱን ትውልድ ሃሳብ የሚያጥላላ ከሆነና፣ ወጣቱ ትውልድ ደግሞ "እነዚህ ከአሮጌው አስተሳሰብ ሊላቀቁ የማይችሉ" ሞት የረሳቸው በማለት ላንጋፋው ትውልድ አስተውሎት ትኩረት የማይሰጠው ከሆነ ግን፣ ማህበረሰቡ በቆመበት ይሄዳል እንጂ የወደፊት ጉዞው አይታሰብም ይሆናል።

ትውልድ እንደ ዱላ ቅብብሎሽ ሩጫ ነው። እያንዳንዱ ሯጭ ዱላውን በጥንቃቄ ይዞና ከተወሰነ ርቀት በኋላ በጉጉት ለሚጠብቀው ሌላ ሯጭ ካላስረከበ ሩጫው ሊጠናቀቅ አይችልም። ዋናው ጉዳይ፣ ዱላውን ሁሌም ካንዱ ሯጭ ወደ ሌላው በጥንቃቄ ማሳለፍ ነው። **አንድ ሯጭ አንዴ የተመደበለትን ርቀት ሮጦ ካጠናቀቀና ዱላውን ለሚቀጥለው ሯጭ ካስረከበ በኋላ ግን እዚያው ባለበት ቆሞ እያጨበጨበ ሩጫ ላይ ላለው ድጋፉን ይሰጣል እንጂ ሩጫውን አይቀጥልበትም።** *ያጋጣሚ* ሆኖ ዱላው በመሃል ላይ ካንዱ ሯጭ እጅ ሊወድቅ ይችላል፣ ያኔ ሩጫውን እንደገና "ሀ" ብሎ መጀመር ነው እንጂ ዱላው ከወደቀበት ቦታ ጀምሮ ሩጫውን መቀጠል አይችልም። የተለፋበት ያ ሁሉ ርቀት ዋጋ አጣ ማለት ነው። ከዚህ ሁሉ አደጋ ለመዳን፣ ማለትም ዱላው መሃል ላይ ወድቆብን ሩጫውን እንደገና እንደ አዲስ ከመጀመር፣ ዱላውን እንዴት አድርገን በጥንቃቄ እንደምናስተላልፍ በያንዳንዱ ትውልድ መካከል በከበሬታና በአንክሮ ላይ የተመሰረተ ውይይትና መግባባት መኖር ያስፈልጋል። ስለሆነም፣ የኔ ትውልዶች ሚና ጋቢያችንን ለብሰን በክብር ቁጭ ካልንበት ጥግ፣ በትግል ዘመናችን የተጎናጸፍናቸውን ድሎች፣ የስኬቶቻችንን ስልትና የተሳሳትንባቸውን መንገዶች ተመልሰው እንዳይሄዱበት ለወጣቱ ትውልድ ከማጋራት ሌላ፣ ባለቀ ጉልበት ሯጭ ሆኖ ለማሸነፍ መሞከር ስህተት ነው ባይ ነኝ። የኛን ዘመን እሴት እንደ ራሳቸው እሴት አድርገው ያላንዳች መሸራረፍ እንዲጠቀሙበት በወጣቱ ትውልድ ላይ ጫና ማሳደሩም የተፈጥሮን ሕግ መጣስ እንደሆነ መረዳት ያለብን ይመስለኛል። ጉልበት በነበረን ዘመን ሮጠን ያስመዘገብነው ፍጥነት አመርቂ ሆኖ ለሜዳልያ ባያበቃንም፣ የተመደበልንን ርቀት ሮጠን አጠናቅቀናልና ዱላውን ለሚቀጥለው ሯጭ አስረክበን የሚቀጥለው ሯጭ ደግሞ ከኛ በተሻለ ፍጥነት ሩጫውን አጠናቅቆ ለሜዳልያ እንዲበቃ በተቻለን ሁሉ መደገፍ ታሪካዊ ግዴታችን መሆኑን አንርሳ ባይ ነኝ! ማለዳ ላይ የመጣውን "ጉልበት" እና አመሻሽቶ የሚደርሰውን "አስተውሎት" አገናኝቶ ለማህበረሰቡ ጥቅም ማዋል ማለት ከዚህ የተለየ ትርጉም የለውም። ሁለቱን ክስተቶችን አገናኝተን የተደቀኑብንን ተግዳሮቶች በአሸናፊነት እንድንወጣ ፈጣሪያችን አስተውሎትን አብዝቶ ይስጠን።

******

*ጀኔቫ፣ 6 ሰኔ 2018 ዓ/ም*

wakwoya2016@gmail.com